# የምስራቁ ድል በሰሜኑ...

Dejat Kassa

02/01/07

ዓይጋ ፎረም የሶማሊያ ኣክራሪ ሃይል ባስተናገድንበት መንገድ ሻዕቢያንም ማስተናገዱ ላይ ሃሳብ እንዲሰጥበት ጥሪ ማቅረቡ ይታውሳል። በዚህም መሰረት የተለያዩ ሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን በተመሳሳይ መንገድ መስተናገድ ኣለበት የሚሉ ኣስተያየት ሰጪዎች ይበዛሉ። እነዚህ ኣስተሳሰቦች መሰረት በማድረግ በሃገር ደረጃና በእያንዳንዱ ዜጋ ደረጃ ምን ማድረግ እንዳለብን ኣስተያየት ለመስጠት እሞክራለሁኝ።

በቅድሚያ የኢትዮጵያ የደህንነት ኣደጋዎች ምን ምን እንደሆኑ መለየት ያስፈልጋል። በዚህ ፅሁፍ ፀሃፊ እምነት የኢትዮጵያ የደህንነት ኣደጋ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው።

## 1. ለእስልምና መስፋፋት ደንቃራ መሆናችን

ማናቸውም ሃይማኖቶች በዙ ተከታዮች ይኖራቸው ዘንድ የተለያዩ የስብከት (በኔ ኣመለካከት ከፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ ለይቼ ኣላየውም) ስራዎች ይሰራሉ። ከዚህም ባሻገር ህዝቦች የኣንድን ሃይማኖት ተከታይ ለማድርግ በሃይማኖት ተስፋፊዎች የሚወሰዱ ሶስት መንገዶች እናያለን። ኣንደኛ ህዝቦችን በጥቅም በመደለል (ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች በማቅረብ) ተከታዮችን የማፍራት መንገድ ነው። ሁለተኛ ሃይማኖትን የፖለቲካ መሳሪያ በማድረግ በኣንድ ኣገር የሚኖሩ ህዝቦች ኣንድ ሃይማኖት እንዲከተሉ የማስገደድ መንገድ ነው። ለምሳሌ የሸሪዓ ህግ ከሚከተሉ ኣገራት ለኣብነት ሱዳንን ብንወስድ የሸሪዓን ህግ የኣገሪቱ የሲቪል ህግ ተክቶ እንዲሰራ የተወሰደበት ዋናው ምክንያት የእስልምና ሃይማኖት የማይከተሉትን ህዝቦች በሃይል የዚህ እምነት ተከታዮች ለማድረግ የተወሰደ ነው። ሶስተኛ ደግሞ በሃይል (በሰይፍ) የኣንድን ሃይማኖት ተከታይ የማድረግ ኢሰብኣዊ መንገድ ነው።

የሱዳንን ከሲቪል ህግ ወደ ሸሪዓ ህግ መቀየር የሱዳን እስላማዊ መንግስት ፍላጎትና ጥረት ብቻ ነበር ብዬ ኣላምንም። ከዚያ በኋላ የተከሰቱትና በደቡብ ሱዳን ክርስቲያኖች የተፈፀሙት የዘር ማጥፋት ወንጀሎች በሱዳን መንግስት ብቻ የተከናወኑ፣ የሱዳን መንግስት ኣጀንዳዎች ብቻ ነበሩ ብባል ለማመን ያስቸግረኛል። ይህ እስልምናን ከሰሃራ በታች በስፋት ለማዝለቅ የመጀመሪያ የዓረቡ ዓለም ሴራ ይመስለኛል። የደቡብ ሱዳንና የዳርፉር እልቂቶች ጉዳይ በጥሞና ካጠናን እስልምናን ወደ ታች እንዳይስፋፋ ደንቃራ በመሆናቸው የከፈሉትና እየከፈሉት ያለ መስዋእትነት ይመስለኛል።

እስልምናን ከሰሃራ በታች ለማዝቅ ቀላሉና ውጤታማ መንገድ ግን ክርስትናን ከኢትዮጵያ ማጥፋት ወይም ማዳከም ነው። ኣፍሪቃን የእስልምና እምነት ተከታይ ለማድረግ ኣውራ ጎዳናው በኢትዮጵያ መገንባት ኣለበት የሚል ኣስተሳሰብ በዓረቡ ዓለም ያለ ይመስለኛል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ ከተዳከመ እስልምናን ወደ ሰሃራ በስተደቡብ ማስፋፋት ቀላል የሸርሸር ጉዞ እንደሚሆን ግልፅ ነው።

ይኸንን ዓላማ ላነገቡ ጠላቶቻችን ደግሞ ከባዱ ስራ ይኸው ነው። ይሁን እንጂ ይኸንን ዓላማ ዳር ለማድረስ ምን ጊዜም ጥረት ማድረጋቸው የማይቀር ነው። ልዩነቶቻችን የሃብቶቻችን ምንጮች መሆናቸው ቀርቶ ያለመግባባት ምክንያቶች የሆኑ እንደሆነ ጠላቶቻችን ይጠቀሙባቸውና፤ የእስልምና ኣክራሪነት ኣፍሪቃውያንን እርስ በድርስ እያባላ ኬፕታውን ለመድረስ ብዙ ጊዜ ላይወስድበት ይችላል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የድህንነት ፖሊሲ እና ስትራተጂ እንዲሁም የፖለቲካ ኣስተሳሰብ ይኸንን ኣደጋ ኣፅንኦት መስጠት ያለበት ይመስለኛል። ይህ ደግሞ የሁሉም ዜጋ ሃላፊነትና ግዴታ ነው።

## 2. **ድንበር ዘለል ወንዞቻችን**

ባሁኑ ወቅት ህልውናቸው ከኢትዮጵያ በሚፈልቁ ወንዞች የተመሰረቱ ማህበረሰቦች (ሱዳንና ግብፅ) ብዛት ከ120 ሚሊዮን በላይ ነው። ከነዚህ ህዝቦች ጋር ያለን የውሃ ፖለቲካ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ፣ የምናውቀውና የታሪካችን ኣንድ ኣካል ነው። እነዚህ ኣገሮች ኢትዮጵያ ከወንዞቿ ኣንድ ጣሳ ያክል ውሃ እንድትቀዳ የማይፈልጉ መሆናቸው በውል እናውቀዋለን። ኢትዮጵያ ከወንዞችዋ የመጠቀም ኣቅሟና ፍላጎቷ ሲያድግ ጠላቶቻችን ተፅእኖኣቸው ክፍ ማድረጋቸው የማይቀር ነው። ምክንያቱም የሱዳንና የግብፅ የደህንነትና የህልውና ኣደጋ (በነሱ ኣስተሳሰብ) ከጣሳ በላይ ሊቀዳ የሚችል ኣቅም ያለው ብዙ ህዝብ በኢትዮጵያ ምድር እውን መሆን ነው። እነዚህ ኣገሮች እንደ ኣደጋ የሚቆጥሩት (ወንዞችን መጠቀም የሚችል ብዙ ህዝብ) ደግሞ ከሚያስቡትና ከገመቱት ፍጥነት በላይ እውን እየሆነ ይገኛል።

እነዚህ ኣገሮች በዓረቡ ዓለም ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው ናቸው። የዓረቡን ዓለም ፀረ-ኢትዮጵያ ኣቋም እንዲኖረው፣ ከዛም ኣልፎ በፀረ-ኢትዮጵያ ተግባራዊ እንርስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፍ በማድረግ የተሳካ ስራ ስንደሰሩ የታሪካችን ኣካል ሆኖ እናውቀዋለን። ከዛም ኣልፎ ኣክራሪነትንና ሽብርተኝነት ለፀረ-ኢትዮጵያ ኣጀንዳቸው እየተጠቀሙበት እያየን ነው። በኢትዮጵያ የደህንነትና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ከሱዳንና ግብፅ በኩል ሊመጣ የሚችል ማናቸውም ኣደጋና ተፅእኖ እንደ ቁልፍ ጉዳይ መወሰድ ኣለበት። የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለነዚህ ሃይሎች ክፍተት የሚሰጥ መሆን የለበትም።

ይኸንን ክፍተት የሚደፈነው ደግሞ የኢትዮጵያውያን ኣንድነት የሚያጠናክር የፖለቲካና የደህንነት ስትራተጂ ሲኖረን ነው። በኢትዮጵያውያን መካከል ያሉ ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶች የፖለቲካ ማስፈራሪያ (ስኬር ታክቲክ) መሆናቸው መቅረት ኣለበት። በኢትዮጵያውያን መካከል ያሉ ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶች ከሚፈለገው በላይ ማክረር ወይም ማደበዘዝ ጠቃሚ ኣይደለም።

ተፈጥሮኣዊ ለዩነቶቻችን ከሚፈለገው በላይ የሚያከሩና ከሚፈለገው በላይ የሚያደበዝዙ የፖለቲካ ኣካሄዶችና ኣስተሳሰቦች ውጤታቸው ኣንድና ኣንድ ነው። የኢትዮጵያውያን ኣንድነት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ኣደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸው። እንደነዚ ዓይነቶቹ ኣስተሳሰቦትና ኣካሄዶች እኛን ለመከፋፈል ለሚያልሙ ጠላቶቻችን ታላቅ ስጦታ ነው። ኢትዮጵያ በኣምስት ወይም ስድስት ትናንሽ ‘ኣገሮች’ ብትከፋፈል፣ የተከፋፈሉት ‘ኣገሮች’ በክልላቸው ውስጥ ያሉትን ውሃዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ኣቅም ኣይኖራቸውም። ኣቅሙ የሚኖራቸውም ውሃው ከሚፈልጉት በላይ ስለሚሆን ‘ዓባይ ዓባይ ኣንተ ኮብላይ’ እየተዘፈነ መሽኘቱ ይቀጥላል። ሱዳንና ግብፅ የዓባይ ልጆች የህልውናቸውና የደህንነታቸው ኣደጋ እስከሆኑ ድረስ፤ ወንዞቻችን የደህንነታችን ኣደጋ ምንጭ ሆነው መቀጠላቸው የማይቀር ነው። ኢትዮጵያውን ይኽንን እውነታን ከፍተኛ ሚዛን የሰጠ የደህንነትና የፖለቲካ ዶክትሪን ሊኖረን ይገባል።

## 3. **ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶቻችን**

ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶቻችን እስልምናን ለማስፋፋትና (በሃይል) ወንዞቻቸንን በብቸኝነት ለመጠቀም ለሚያልሙት ጠላቶቻችን መሳሪያ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማሳየት ተሞክሯል።

ልዩነቶቻችን ማንም ሊቀይራቸው የማይችሉ በፈተፈጥሮ የተሰጡን ሃብቶቻችን ናቸው። ይሁን እንጂ በኛ ምርጫ ወይም ፍላጎት ያልተፈጠሩትን ልዩነቶቻችን ተቀብለን ወደፊት ላለመራመድ እያንገራገርን እንገኛለን። ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶች በጊዜ ሂደትና ክስተቶች ምክንያት ሰው ሰራሽ ልዩነቶች እየታከሉባቸው፣ ከተፈጥሮኣዊ ልዩነቶቻችን ወደ ኣክራሪና ፅንፈኛ ልዩነቶች ለማሸጋጋር የምኳትን ቀላሎች ኣይደለንም።ይህ ደግሞ ለጠላቶቻችን ከፍተኛ ክፍተት ነው።

ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶቻችንን ኣክራሪነትና ፅንፈኝነት የሚያላብስ የፖለቲካ ኣካሄድና ኣስተሳሰብ ከስሩ መነቀል ኣለበት። በኢትዮጵያውያን መሃከል ያሉ ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶች ከመንግስትነትና ከፖለቲካ ጋር መተሳሰራቸው ኣዲስ ክስተት ኣይደለም። ኢትዮጵያን የገዙ ወይም ያስተዳደሩ ነገስታት/መንግስታት ወደ ስልጣን የሚመጡት ከተወሰነ ኣከባቢ (ብሄረሰብ፣ ብሄር፣ ክልል፣ እምነት) በሚያገኙት የፖለቲካ፣ የወታደራዊና የሎጂስቲክ ድጋፍ መሆኑ ታሪካችን ይመሰክራል። ይህ ታሪካዊ እውነታ ፅነፈኛ የፖለቲካ ኣስተሳሰብ እየፈጠረ ነው። የፖለቲካ ስልጣንን በዚህ መንገድ የማግኘት ታሪክ እንዲያከትም የተጀመሩት እርምጃዎች ለመናድ ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶቻችን ጥቅም ላይ ሲውሉ ተመልክተናል። ተፈጥሮኣዊ ለዩነቶቻችን የፖለቲካ ስልጣንን ከመቀዳጀት ጋር ያላቸው ቁርኝት መሰበር ኣለበት። ይህ ኣካሄድ ወደ ጤነኛ፣ ኣሳታፊና ገንቢ ኣካሄድ መቀየር እንዳለብን የሚያግባባ ይመስለኛል። የዚህ ኣካሄድ የመጀመሪያው እርምጃ በእያንዳንዳችን ያሉ ማናቸውም ዓይነት ተፈጥሮኣዊ ልዩነቶች መቀበልና ማክበርን ይጠይቃል። በዚህ መንገድ መራመድ ስንጀምር ችግሮቻችን ለመፍታት ኣያዳግተንም። ከዚሁ ኣማራጭ በተፃራሪ መንገድ ስንሄድ መሽነፋችን ኣይቀርም።

በመጀመሪያ ደረጃ ልዩነትን ሳይቀበሉና ሳያከብሩ ስለዴሞክራሲ ማውራት ሽፍጥ ነው። ስለ ፍትህ፣ ነፃነትና እኩልነት እንታገላለን ካልን የትግላችን መጀመሪያ ልዩነትን መቀበልና ማክበርን ይሆናል። የኣንድን ህዝብ ማንነት (ከሌላው ህዝብ ልዩ የሚያደርገውን) ሳንቀበልና



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሳናከብር ስንቀር፣ መብቱ የተገፋው ህዝብ የፅንፈኝነትና አክራሪነት ፖለቲካ ሊያራምድ ይችላል። እንደዚህ አይነት የፖለቲካ አካሄድ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን አይበጅም። እንደዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ አስተሳሰብና አካሄድ እንዳይፈጠር መታገል አለብን። ምክንያትም አመጪም መሆን የለብንም። አክራሪነትና ፅንፈኝነት የተላበሱ የፖለቲካ አስተሳሰቦችና አካሄዶች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ምክንያት ከሚሆኑ እንቅስቃሴዎች መታቀብ አለብን። ያንን ባለማድረጋችን የከፈልነው ኪሳራ መዘንጋት የለብንም።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያውያን ያልተማርንበትና የዘነጋነው አንድ ታሪክ አለን። ተፈጥሮ መረብ ምላሽን የኢትዮጵያ አካል አድርጋ ፈጠረች። ጊዜና ክስተት መረብ ምላሽን ከኢትዮጵያ ለይቶ ኤርትራን ፈጠረ። ይህ ክስተት ኤርትራውያን ከኢትዮጵያን የተለዩ የሚያደርጋቸው የታሪክ ባለቤት አደረጋቸው። ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን ተለይተው በኖሩበት ወቅት የተፈጠረ ልዩነታቸውን ወይም በዚህ ክስተት ምክንያት ያገኙትን ጥቅም (ራስ ገዝን) ጠብቀው ከኢትዮጵያ ጋር ለመኖር ወሰኑ። በኢትዮጵያውያን ደግሞ ከኛ ጋር ምንም ልዩነት ሳይኖራችሁ መኖር አለባችሁ ብለን አስገደድን። ይህ የመብት ረገጣ አክራሪነትና ፅንፈኝነትን ወለደ። ልዩነትን አለመቀበልና አለማክበር ለሶስት ዓስርት ዓመታት አዋግቶ አለያየን። ተለያየተንም ሰላም አጣን።

እዚህ ላይ አንድ ቁልፍ ቁም ነገር ማየት አለብን። በኤርትራና በኢትዮጵያ ውህደት ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ፍላጎት ቢኖርና ተሞክሮም ቢሆን ታሪካዊ ጠላቶቻችን በብርሃን ፍጥነት ችግሩ በእጃቸው አስገብተው ስላወሳሰቡት መግባባት ላይ ይደረስ ነበር ብዬ አላስብም። ስለዚህ ልዩነቶቻችን በመግባባት፣ በመተማመን፣ በመከባበር፣ በመፈቃቀር፣ በብልሃት፣ በከፍተኛ የአገራዊ ስሜትና አርበኝነት ማስተናገድ የሚያስችል የፖለቲካ አካሄድ መከተል የደህንነታችንና የህልውናችን ቁልፍ እርምጃ ነው።

## 4. በትናንሽና ደካማ አገሮች መከበባችን

በኤርትራ፣ በሶማሊያና በጁቡቲ መከበባችን ከመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ በላይ ፖለቲካዊ ፋይዳ አለው። አንደኛ እነዚህ አገሮች ግራም ነፈሰ ቀኝ በማናቸውም ነገር የኢትዮጵያ ጥገኞች ናቸው። ለወደፊቱም ጥገኝነታቸው እያየለ ስለሚሄድ ከኢትዮጵያ ጋር ዘርፈ ብዙ ትስስር ካልፈጠሩ መኖር ይቸግራቸዋል ወይም አይችሉም። እነዚህ አገሮች ከኢትዮጵያ ጋር ዘርፈ ብዙ ትስስር ማድረግ ካልፈለጉ ወይም ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ዓይነት ትስስር እንዲፈጠር ካልፈለግን/ካላደረግን፤ አገሮቹ ቀውስ ውስጥ የዘፈቃሉ። እነዚህ አገሮች ቀውስ ውስጥ ከገቡ ደግሞ ለኢትዮጵያ ጠላቶች መሸጋገሪያ ድልድይ ይሆናሉ። ኤርትራና ሶማሊያ ከሁለተኛ ዓለም ጦርነት ማብቂያ ጀምሮ አንዴ በቀውስ አንዴ ደግሞ በቀውስና በርጋታ መሃል በመዝለቃቸው ለኢትዮጵያ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለማጥቃት መሸጋገሪያ ድልድይ ሆነው ኖረዋል።

ለምሳሌ የሶማሊያን ጉዳይ እንይ። የኤርትራ ጉዳይ የታሪካችን አካል ሆኖ የምናውቀው ነው። በ1990ዎቹ (እጎአ) መጀመሪያ በሶማሊያ የፖለቲካና የጎሳ ተቀናቃኞት መካከል በሶደሬ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የተደረገው ድርድር ጋት ሳይሄድ የበተኑት ግብፆች ናቸው። ሶማሊያ መግስት አልባ በመሆንዋ ደግሞ የፀረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ስትራተጂያዊ ቀጠና ሆና ቆይታለች። እኛም የሽብርተኝነት ሰለባ ሆነናል። ማሳረጊያውም ሳንወድ ጦርነት አስተናግደናል።

ስለዚህ የከበቡንን አገሮች የተረጋጉና ሰላም የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ቀናና ብልህ የውጭ ግኑኝነት መርህ አለን ማለቱ በፍፁም በቂ አይደለም። ይህ ጉዳይ የውስጥ የፖለቲካ አካሄዳችን አስተሳሰባችን አካል መሆን አለበት። በነዚህ አገሮች የሚከሰቱ ቀውሶች ለኢትዮጵያ ትልልቅ አደጋዎች ናቸው። እንዚህ አገሮች ደግሞ በኢትዮጵያ ጠላቶች ጣልቃገብነት በቀላሉ ቀውስ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። በነዚህ አገሮች ቀውሶችና አለመረጋጋቶች እንዳይከሰቱ መከላከል የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ስራ መሆን አለበት።

ከላይ የተዘረዘሩት አራት የድህንነታችን የአደጋ ምንጮች ጋር በማዛመድ ተፈጥሮአዊ ልዩነቶቻችን በቀናነትና በአግባቡ ማስናገድ የሚያስችል የፖለቲካና የደህንነት ስትራተጂ ሊኖረን እንደሚደባ ለማመልከት ተሞክሯል። እዚህ ላይ ተጨማሪ መፍትሄዎች በማመልከት የዚህ ፅሁፍ መንደርደሪያ የሆነውን የሻዕቢያ ጉዳይ በአጭሩ ለማሳየት ይሞከራል።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን ግብፅ፣ ሱዳንና የነዚህ አገሮች ቶፎዞዎች የዓረብ መንግስታት መሆናቸው ለኢትዮጵያዊያን ግልፅ ነው። በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የጠላቶቻችን ስትራተጂ እኛን አቅመቢስ አድርጎ በድህነት እንድንዳክር ማድረግ ነው ተብሎ ይነገራል። ይሁን እንጂ ከዛ በላይ መግፋት ስላልቻሉ እንጂ፣ የመጨረሻው ግባቸው ኢትዮጵያን መበታተን ነው። በድህነት ማቆየት የሚል ስትራተጂ ነበረ እንኳን ቢባል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በሚያስፈራ ፍጥነት እያደገ በመጣበትና የኢኮኖሚ አቅሙም ተስፋ በሚሰጥ መልኩ እያደገ ባለበት ባሁኑ ወቅት እንደዋና ስትራተጂ ይከተሉታል ተብሎ መታሰብ የለበትም። ስለዚህ መፍትሄዎቻችን ይህን እውነታ ማገናዘብ አለባቸው።

ዋናው መፈትሄ መንግስት፣ ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ወይም መከላኪያ ሰራዊት ብቻ በሚያደርጉት ስራ ወይም ወታደራዊ ፍልሚያ የሚመጣ አይደለም። ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጦር ሜዳ ሄደው ተታኩሰው ጠላትን ያስወግዱ ካልን እነዚያ ውንድሞቻችንና እህቶታችን የሚሰሩትን ስራ ለመስራት ዝግጁም ፈቃደኛም መሆን አለብን። የጦርነት አማራጭ የምንወስድ ሰዎች መጀመሪያ ራሳችንን ወታደራዊ ደንብ ልብስ አልብሰን እናስብ። 180 ሽህ መከላኪያ ሰራዊታችን ከዚያ ወደዚያ እያልን የወገኖቻችንን ህይወት አደጋ ላይ ከምንከት አስተማማኝ ድል ሊያጎናፅፉን የሚችሉ ሌሎች አማራጨች አሉን። በዚህ ፅሁፍ ፀሃፊ እምነት የሚከተሉት ውጤታማ መፍትሄዎች ናቸው።

## ሀ. ኢኮኖሚያዊ አቅም መፍጠር

መጀመሪያው መፈትሄ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት በአጭር ጊዜ ማስመዝገብ ነው። ጠላቶቻችን ራሳቸው በለኰሱዋቸው እሳቶች እየተቃጠሉ ባሉበት ወቅት ኢጋጣሚውን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ተጠቅመን ከፍተኛ የኢኮኖሚ እምርታ ማስመዝገብ አለብን። ይህ እንደ ጦርነት እናስበውና በዚህ ፍልሚያ ውስጥ የኔ ሚና ምን ቢሆን ነው አጋዥ የሚሆነው ብለን እናስብ፤ የምንችለውን እናድርግ።

በመጀመሪያ ደረጃ ማንኛውም ደካማ አገርና ቡዱን ነጋ ጠባ በኛ ላይ ጦርነት የሚያውጀውና የሚያልመው፤ ኢትዮጵያውያን ድሆችና በቀላሉ ሊሸነፉ የሚችሉ ናቸው ብለው ስለሚያስቡ ይመስለኛል። ኢኮኖሚያዊ አቅም ወታደራዊ አቅምን ይፈጥራል። ኢኮኖሚያዊ አቅም ብዙ ወዳጅ (በሰጥቶ መቀበል መርህም ቢሆን) ይፈጥራል፤ ጠላቶችም ደጋግመው እንዲያስቡ ያደርጋል። ኢኮኖሚያዊ አቅም የኢትዮጵያውያንን አንድነት ያጠናክራል። የኢትዮጵያውያን አንድነት ማጠናከር ደግሞ የጠላቶቻችን ማሽሎኪያ ቀዳዳ መቀርቀር ነው።

ባደጉት አገሮች የምትገኙ ወገኖች አንድ ነገር እናስብ። የኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ማደግ የህልውና ጉዳይ ስለሆነ ታድጋለች። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ እድገት የዜጎቿ እድገት ድምር ውጤት መሆን አለበት። ኢትዮጵያውያን አብረው ማገድ አለባቸው። ዙምባቡዌ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት እምርታ አሳይታ ነበር። ልጆቿ ግን አብረው ባለማደጋቸው፤ ሃብታም ያደረጓት በአዳን ገንዘባቸውን ወደ አገሮቻቸው ባንኮች ሲያሻግሩት እንጦርጦስ ወረደች። ኬንያ ከኢትዮጵያ ትሻላለት። ኬንያውያን ከኤትዮጵያውያን ይሻላሉ ወይ ሌላ ነገር ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ እድገት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እድገት ድምር ውጤት እንዲሆን ጊዜያችን እውቀታችንንና ገንዘባችን መጠቀም አለብን። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ካደግን የጠላቶቻችን ታሪካዊ ህልም የማምከን አቅም ይኖረናል።

## ለ. ወታደራዊ አቅም መፍጠር

በአንድ ወታደራዊ ፍልሚያ ውስጥ የምንከፍለው ኢኮኖሚያዊ፣ ሰብአዊና የጊዜ ሃብት መካላከያ አቅማችንን ልናጎለብትበትና ሳንታኮስ ጠላትን እንዳይተናኮለን ማድረግ እንችላለን። የአደጋ በሮቻችን ጊዜ የሚጠይቀው ቴክኖሎጂና እውቀት የሚጠቀም መከላኪያ በማነፅ ሳንታኮስ መጠበቅ እንችላለን። እንደዚህ ዓይነት ብቃት ያለው ሃይል ለመፍጠር ደግሞ የኢኮኖሚ አቅም ያስፈልጋል። ወታደራዊ አቅማችን ኢትዮጵያን ከመጠቀም ያለፈ ስራ መስራት የሚችል መሆን አለበት።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ወደ 80 ሚሊዮን የሚጠጋ ሲሆን፤ የሶማሊያ፣ የኤርትራና የጂቡቲ ህዝብ ቁጥር ደግሞ 14 ሚሊዮን ገደማ ነው። ከ40 ዓመት በኋለ የኢትዮጵያ ህዝብ 145 ሚሊዮን ደገማ እንደሚያክል ሲገመት፤ የኤርትራ 10 ሚሊዮን፣ የጂቡቲ 1 ሚሊዮን የሶማሊያ 25 ሚሊዮን ይሆናል ተብሎ ይገመታል። የፖለቲካና የደህንነት ስትራተጂያችን የ5ና የ10 ዓመታት መሆን የለባቸውም። ወጥና ከኢትዮጵያ ድህንነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ማናቸውንም ጥቃቅን ነገሮች ሳይቀር ግምት ውስጥ የሚከት፤ በየጊዜው የሚያጋጥሙ ክስተቶች ለማስተናገድ የሚያስችል ተለጣጭ (ኢላስቲክ) ስትራተጂ ሊኖሮን ይገባል። ከ145 ሚሊዮን በላይ የሚያክሉ ህዝቦች ዛላንበሳ፣ ቡሬ፣ ጅጅጋና ቀብሪ ደሃር ምሽግ ገንብተው፤ በ5ና በ10



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዓመት የድህንነት ስትራተጂ የፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነታቸው ሊጠብቁ አይችሉም። ይህንን እውነታ ግምት ውስጥ የከተተ ስትራተጂ ያስፈልጋል። ይህን ግምት ውስጥ የሚከት የመከላኪያ አቅም መገንባት መጀመር አለብን።

## ሐ. ከጎረቤቶቻችን ሁለገብ ትስስር ማድረግ

ቀደም ሲል ኢትዮጵያን የከበቡዋት አገሮች እንደ አገር ተረጋግተው ለመዝለቅ ከኢትዮጵያ ጋር ጤነኛ ትስስር መፍጠር እንዳለባቸው ለማመልከት ተሞክሯል። የአንድ አገር ህዝብ በሰላም ከኖረ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት እያስመዘገበ ይሄዳል። የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገቱ ስያሻቅብ ደግሞ ፍላጎቱ እየጨመረ ይሄዳል። ፍላጎቱ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ደግሞ ሰላሙና እድገቱ አደጋ ላይ በሚጥል ፍላጎቱንም የሚያሳጣ አማራጭ አይከተልም።

በዚህ መልኩ ሶማሊያና ኤርትራ ወደተሻለ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መረጋጋት እንዲሁም የኢኮኖሚና እድገት ከተሸጋገሩ እኛን የሚተናኮሉ አይሆኑም። በነገራችን ላይ እነዚህ አገሮች ወደ ተሻለ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም መሸጋገር ከኢትዮጵያ ጋር በሚፈጥሩት ጤነኛ ትስስር ላይ ይመሰረታል። የኤርትራና የሶማሊያ ህዝቦች ፍላጎት ከዚህ የዘለለ አይሆንም። የኢትዮጵያውያንም ፍላጎት ከዚህ የተለየ መሆን የለበትም።

ይሁን እንጂ ታሪካዊ ጠላቶቻችን በኛና በጎረቤቶቻችን በፍፁም መተማመንና መግባባት የተመሰረተ ትስስር እንዲፈጠር አይፈልጉም። በጎረቤቶቻችን ያለው ቀውስ እንዲቀጥልና እንዲባባስ ነው የሚፈልጉት። ወደ ተሻለ መረጋጋት ቢሸጋገሩም እንኳ በማንኛውም ጊዜ እንዲፈርሱ ሊያደርጋቸው ይችላሉ። በቀላሉ ፈርሰው (እንደ ሶማሊያ) የችግራችን ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህ አገሮች በጠላቶቻችን ሴራ አደጋ ላይ እንዳይወድቁ የመጠበቅም ሃላፊነት ያለብን ይመስለኛል። ይህንን ለማድረግ በዙ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ። አንዱና ቀላሉ ኢኮኖሚያቸው በኛ ኢኮኖሚ ላይ ጥገኛ እንዲሆን ማድረግ ነው። ለዚህ ድል ቁልፍ የትግል አቅጣጫ ደግሞ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የመገንባት አቅጣጫ ነው።

## መ. አሰተማማኝ የባህር በር ማግኘት

በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፖለቲከኞች፣ ፈላስፎች፣ የህግ ባለሙያዎች፣ የታሪክ ባለሙያዎች እንዲሁም ተራ ዜጎች የባህር በራችን አላግባብ እንዳጣን ለማስረዳት ይሞክራሉ። ይህ ጉዳይ በኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ታላቅ የፖለቲካ መነሻ እየሆነ እያየን ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ አንደኞችን የባህር በራችን ያላግባብ አጥተናል የምንል ስንሆን፤ ሌሎቻችን ደግሞ የለም የባህር በር አልነበረንም፤ ያልነበረንም አላጣንም የምንል ነን። እውነቱ ግን ከሁለቱ አንዱ ነው። ኢትዮጵያውያን እውነቱ የትኛው እንደሆነ ማወቅና በጉዳዩ ላይ መግባባት ላይ መድረስ አለብን። ይኸንን ጉዳይ ከፖለቲካ ወገንተኝነት በፀዳ መልኩ መፍታት አለብን። ካልተፈታ ግን ችግሩ ዘለአለማዊ ይመስላኛል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የራሳችን የባህር በር እንዲኖረን የሚያስገድዱ ሁኔታዎች በያንዳንዷ ቀን እያየን ነው። እዚህ ላይ በግልፅ መቀመጥ ያለበት ጉዳይ ኢትዮጵያውያን የባህር በር ኣልነበረንም የሚሉ ወገኖች ኣገሪቷ በመምራት ያሉ ናቸው። የባህር በር ባይኖረንም ግን ኣስተማማኝ፣ ዘላቂ፤ የኣፍሪቃ ቀንድ ቀጠና ፖለቲካ በተቀየረ ቁጥር የማይናወጥ የህግ ከላለ ባለው መንገድ የባህር በር የመጠቀም መብት እንዲኖረን መስራት ይጠበቅባቸዋል። የዓባይን ተፋሰስ ከዓባይ ተፋሰስ ኣገሮች ጋር (ጠላቶቻችንም ጭምር) ነጋ ጠባ ድርድርና ፈቃድ የምንጠይቀው እነዚያ ኣገሮች ለወንዞቻችን ያላቸው ባለቤትነት እኛ ለቀይባህርና ለህንድ ውቅያኖስ ሊኖረን ከሚችል ባለቤትነት የበለጠ ስለሆነ ኣይደለም። የህግ፣ የሰብኣዊነትና የሞራል ግዴታ ስለሆነ ነው። ዓባይን በጋራ ባለመጠቀም የሱዳንና የግብፅ (120 ሚሊዮን) ህዝቦች ህልውና ኣደጋ መክተት ከህግ፣ ከሰብኣዊነትና ከሞራል ኣግባብ ኣይደለም ከተባለ ደግሞ የ80 ሚሊዮን ህዝባችን ህልውናም ኣደጋ ላይ መክተት ከህግ፣ ከሰብኣዊነትና ከሞራል ኣንፃር ትክክል ኣይደለም።

ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት የህልውናችንና የምስራቅ ኣፍሪካ የሰላም ምንጭ ነው። መጀመሪያ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ባህር በር በከፍተኛ ስፍራ ያለው ነው። በኔ ኣስተሳሰብ የኢትዮጵያ መንግስት ከሶማሊያ ኣክራሪ ሃይሎች ጋር ወደ ውጊያ የገባው ይህ ቡዱን ኦጋዴንን እቆርሳለሁ ስላለ ኣይደለም። ሽብርተኝነት እንዳይስፋፋም ኣይደለም። ኦነግና ኦብነግ ተፈርቶም ኣይደለም። የፖለቲካ ኣቅጣጫ ለመቀየርም ኣይደለም። ኣሜሪካን ለማስደሰትም ኣይደለም። የሻዕቢያን የጣልቃገብነት ሙከራ ለማክሸፍም ኣይደለም። ዋናው ምክንያት በኣሁኑ ወቅት የምጠቀምባቸው የጁቡቲና የበርበራ ወደቦች በጠላቶቻችን እጅ ገብተው ጉሮሮቻችን ሊዘጋ ኣንድ ሃሙስ ነበር የቀረን። የጂቡቲን የነግብፅ ተባባሪ መሆን ሌላ ምንም ምክንያት ኣልነበረውም።

ስለዚህ የኛ ባህር የለንም ከተባለም የህግ ከለላ ያለው በዘላቂነት ያላንዳች ስጋት ከውጪው ዓለም ጋር የምንገናኝበት ባህር ሊኖረን ይገባል። ጁቡቲ ስታኮርፍ እንዳሻት የምተከለክለውና የምትሰጠው፣ የሶማሊያ የጎሳ መሪ ሲሸፍት እየበረግግን መኖር የለብንም። ይህም ብቻ ሳይሆን የምንጠቀምባቸው ወደቦች የሚጠብቅ የባህር ሃይል ያስፈልገናል። ኣስተማማኝ የባህር በር የለንም ማላት በጠላቶቻችን ዘንድ ምን ጊዜም ደካሞች ነን። በጠላቶቻችን ዘንድ ደካማ ሆነን ከታየን ደግሞ ለጥቃት እንጋለጣለን።

## ሻዕቢያን በጦርነት የማስወገድ ጉዳይ

ኢትዮጵያውያን ጠላትን የመመከትና ከጠላት የሚቃጣብንን ኣደጋ በማምከን እንቅስቃሴኣችን ውስጥ የሚከተሉትን ቁም ነገሮች ግምት ውስጥ መክተት ኣለብን። ኣንደኛ ዋናው ኣደጋ ባግባቡ መለየት። ሁለተኛ የተቃጣብንን ኣደጋ በሚገባ መልኩ ሊቀለብስ የሚችል ኣካሄድ መለየት። ሶስተኛ ሌሎች ወገኖችም ሊያስተምር የሚችል እርምጃ መውሰድ። ኣራተኛ ጠላትን የሚቀንስና ወዳጅን የሚያፈራ እርምጃ መከተል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሻዕቢያን ለመደምሰስ የሚወስድብን ጊዜ ኣጭር ሊሆን ስለሚችል ብቻ መከተል ያለበን ኣማራጭ ኣይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሻዕቢያ የትላልቆቹ ጠላቶቻችን መሳሪያ እንጂ የኤርትራ ህዝብ ጠበቃ ሆኖ ኣይደለም ከኢትዮጵያ ጋር ውጥረት ውስጥ የተዘፈቀው። የኤርትራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ሊጣላበት የሚችል መነሻ ኖሮት ሳይሆን የግብፅና የቲፎዞዎችዋ ቆሻሻ ስራ እንዲሰራ በሻዕቢያ ስለተገደደ ነው። ሻዕቢያን በማጥፋት ደግሞ የነግብፅ ኩሬ ማደረቅን ኣይቻልም። ይልቁንስ የኤርትራ ህዝብ ኢትዮጵያን የሚጠላበት ተጨማሪ ምክንያት መፍጠር ነው። ጠላት የሚያበዛ እርምጃ ነው።

ከዚህም ባሻገር የኢትዮጵያ የመጨረሻው የፖለቲካና የደህንነት ስትራተጂ ከጎረቤቶቿ ጋር በመተማመንና በመግባባት ላይ የተመሰረተ ትስስር መፍጠር መሆን እንደሚገባ ለማመልከት ተሞክሯል። ስለዚህ ጦርነት ማድረግ ያለብን ሻዕቢያን ድል ለማድረግ ሳይሆን የኤርትራዊያንን የተዛቡ ኣስተሳሰቦችን ድል ለማድረግ መሆን ኣለበት። የኤርትራ ህዝብ ችግር ለኛም ተርፎ እየጎዳን ያለው በተዛቡ ኣስተሳሰቦች ምክንያት ነው።

የመጀመሪያውና ዋናው ቁም ነገር ኤርትራዊያን በነፃነት ትግል ስም ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች መስዋእት እንደሆኑና ከተለዩ በኋለም ቀውስ ውስጥ እየከተቱዋቸው መሆናቸውን መገንዘብ ኣለባቸው። ሁለተኛ ኢትዮጵያ ኣንገቷ ተቆርጦ መኖር ኣትችልም የሚለው ኣስተሳሰባቸው ውድቅ መሆኑና ይልቁንስ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተለይታ መኖር ትችል እንደሆነ ለማየት ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። እስካሁን ሁለት ክስተቶች ይኸንን እውነታ እንዲያዩ ኣላስቻሉዋቸውም።

ኣንድኛ ከወረራው በፊት "ኤርትራ የኤርትራዊያን ወንዶች የሚስቶቻቸው ኣገር፣ ኢትዮጵያ የኤርትራዊያን ሴቶች የባሎቻቸው ኣገር" እያሉ ከኢትዮጵያ ሃብት ይሰበስቡ ስለነበርና፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተለይታ (በኢኮኖሚ) ስላላዩ እስከዛ ጊዜ ድረስ ችግሩን ኣልገባቸውም። ከወረራው በኋላም የመቸገራቸው ምክንያት ጦርነቱና ህግደፍ እንደሆኑ እንጂ መለየታቸው መሆኑ ለመገንዘብ ጊዜ ኣላገኙም። ሻዕቢያ በራሱ ከስሞ ወይም በራሳቸው በኤርትራውያን ተወግዶ፤ ኤርትራውያን ባስተማማኝ ሰላም ሆነው ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ግኑኝነት ሳይኖራቸው ለኣንድ ኣስር ኣስራኣምስት ኣመት ቢያዩት ጥሩ ይመስለኛል። ልካቸው ካወቁ በኋላ ከላይ እንደተጠቀሰው በመግባባትና በመተማመን ወደ ተመሰረተ ትስስር መግባት ይቻላል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com